GSMA

# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

## ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

GSMA

GSMA አዎንታዊ የንግድ ከባቢዎችን እና ማህበራዊ ለውጥን የሚያመጡ ፈጠራዎችን ለማነቃቃት የሞባይል ስነ-ምህዳሩን አንድ ያደረገ ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው። ራዕያችን ሰዎች፣ ኢንዱስትሪዎች እና ማህበረሰብ እንዲበለፅጉ የግንኙነትን ሙሉ አቅም ማሳደግ ነው። በመላው የተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች ሥነ-ምህዳር እና በተመሳሳይ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የስልክ አገልግሎት አቅራቢዎችን እና ድርጅቶችን በመወከል፣ GSMA በሦስት ሰፋፊ ዓምዶች ዙሪያ ለአባላቱ የሚከተሉትን ያበረክታል፦ ግንኙነትን ለመልካም ነገር ማዋል፣ የኢንዱስትሪ አገልግሎቶች እና መፍትሔዎች እና ተደራሽነት። ይህ እንቅስቃሴ መመሪያ ማሻሻልን፣ በአሁን ጊዜ ያሉ ትላልቅ የማህበረሰብ ተግዳሮቶችን መቅረፍ፣ ቴክኖሎጂውን እና ተንቀሳቃሽ ስልክ እንዲሠራ የሚያደርግ የበይነመረብ ግንኙነትን መደገፍ እና በMWC እና በM360 ተከታታይ ዝግጅቶች ላይ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች ሥነ-ምህዳሩን ለማሰባሰብ በዓለም ትልቁን መድረክ ማዘጋጀትን ያካትታል።

www.gsma.com ላይ ተጨማሪ እንዲያገኙ እንጋብዝዎታለን

GSMAን በTwitter/X ላይ ይከተሉ፦ @GSMA

## በGSMA የተገናኘ ማህበረሰብ

የተገናኘ ማህበረሰብ ፕሮግራም በማደግ ላይ ባሉ ገበያዎች በቂ አገልግሎት በማያገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በማተኮር የስልክ በይነመረብ ተደራሽነትን እና ማለማመድን ለማሳደግ ከተንቀሳቃሽ ስልክ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ከቴክኖሎጂ ኩባንያዎች፣ ከልማት ማህበረሰቡ እና ከመንግሥት ጋር ይሠራል። ቁልፍ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- በስልክ በይነመረብ ሽፋን እና አጠቃቀም ክፍተት ላይ ግንዛቤዎችን እና ትምህርቶችን ማዘጋጀት እና ማሰራጨት።
- ሽፋን እና አጠቃቀምን ለመጨመር የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎት አቅራቢዎችን መደገፍ።
- የስልክ አገልግሎት አቅራቢዎች የተሻለ የዲጂታል አካታችነት ለማረጋገጥ የሚያደርጉት ጥረት በመንግሥታት፣ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ውጤታማ ድጋፍ እየተደረገለት መሆኑን ለማረጋገጥ የጉትጎታ እና የመመሪያ ዝግጅት ሥራዎችን ማከናወን።

ለበለጠ መረጃ እባክዎ www.gsma.com/connected-society ይጎብኙ

ወይም በሚከተለው አድራሻ ኢሜይል ይላኩልን፦ connectedsociety@gsma.com

# ይህን የክህሎቶች ሥልጠና መርጃ ስብስብ በተመለከተ መግቢያ

ተንቀሳቃሽ ስልኮች ከጥሪ ማድረጊያ መሣሪያነት በላይ ናቸው። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች በይነመረብን የሚያገኙባቸው ዋነኛ መንገዶች የመሆናቸው ጉዳይ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል። በይነመረብ ለተጠቃሚው ብዙ ጥቅሞችን ሊያቀርብ ቢችልም፣ የተንቀሳቃሽ ስልክን በአግባቡ ለመጠቀም የተወሰኑ ክህሎቶች እና እውቀት ይጠይቃል። ይህ ማለት ክህሎቶቹ እና ግንዛቤው የሌላቸው ሰዎች እነዚህን ሕይወት የሚያሻሽሉ አገልግሎቶች መጠቀም አይችሉም ማለት ነው።

## ይህ ሥልጠና መርጃ ስብስብ ምን ለማሳካት እየሞከረ ነው?

ይህ የሥልጠና መርጃ ስብስብ በስልክ በይነመረብ ግንዛቤ ዙሪያ የሰዎችን መሠረታዊ ዕውቀት ለማሳደግ ሥልጠና ማቅረብ ለሚፈልጉ ለተንቀሳቃሽ ስልክ አውታረ መረብ አቅራቢዎች (MNOs)፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች (NGOs)፣ ለልማት ድርጅቶች እና ለመንግስት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

እዚህ የቀረቡት የስልጠና መርጃዎች እና ግብዓቶች አሰልጣኞች በተንቀሳቃሽ ስልኮች ላይ የበይነመረብን ጥቅም እና ተግባራት ለማሳየት የሚፈልጓቸውን ነገሮች ያገኙባቸዋል። በዚህ ምክንያት፣ ሰልጣኞች በይነመረብን ለምን ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ እና አገልግሎቱን ለማግኘት እና ለመጠቀም የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ክህሎቶችን በጥልቀት እንዲገነዘቡ ይደረጋል። ይህም የተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብ ሊያቀርባቸው የሚችላቸው ሕይወትን የሚያሻሽሉ አገልግሎቶች ላይ ያለን ግንዛቤ እና የመጠቀም ሁኔታ እንዲጨምር ያደርጋል ብለን እናምናለን።

በዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ውስጥ የቀረበው ሥልጠና የስልክ በይነመረብ ክህሎታቸው አነስተኛ የሆነ ወይም ምንም ክህሎት የሌላቸው ሰዎችን ታሳቢ ያደረገ ነው። የተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብ ምን እንደሆነ እና በመስመር ላይ እንዴት ግንኙነት ማድረግ እና መፈለግ እንደሚቻል ማወቅ የሚፈልጉ ሰዎችን ለማስተማር ያለመ ነው። ይህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን የመጠቀም ልምድ ለሌላቸው ሰዎች የታሰበ ስላልሆነ፣ እንደ ጥሪ ማድረግ ወይም አጭር የጽሁፍ መልዕክት መላክ ያሉ መሠረታዊ ተግባራትን አያካትትም። በተመሳሳይ፣ ቀድሞውኑ የስልክ በይነመረብን በደንብ ለሚያውቁ ሰዎች የተዘጋጀ አይደለም።

## «እንዴት እንደሚሠራ መመሪያ» የሚለው ምንድን ነው?

«እንዴት እንደሚሠራ መመሪያ» የሚለው ሰነድ ከዚህ ሰነድ ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ መዋል አለበት፣ በዚህም በየትኛውም ሀገር ውስጥ አሰልጣኞች ለታዳሚዎቻቸው በመሠረታዊ

የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች ላይ በተጨባጭ አውድ ላይ የተመሰረተ ሥልጠና እንዲያዘጋጁ እና እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል። መመሪያው ለታዳሚዎቻቸው ተስማሚ፣ ትርጉም ያላቸው የሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎችን እና ግብዓቶችን ለማዘጋጀት የሚወስዷቸውን ድርጊቶች እና ምክሮችን ያቀርባል።

እንዲሁም ይህ እንዴት እንደሚሠራ መመሪያ በዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ውስጥ ከሚገኙ መረጃዎች እና ምክሮች በተጨማሪ በርካታ አጋዥ ምሳሌዎችን ያካትታል። ሁሉም የዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ተጠቃሚዎች የሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎቻቸውን ለማሟላት ከዚያ እንዴት እንደሚሠራ መመሪያ ጋር በጣም ተያያዥ የሆኑትን ክፍሎች እንዲገመግሙ እና እንዲጠቀሙ እናበረታታለን።

## በዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ውስጥ ምን ተካቷል?

ይህ የስልጠና መርጃ ስብስብ በመሰረታዊ ስማርት ስልክ ላይ ስለ በይነመረብ አጠቃቀም መግቢያን ያቀርባል። ሰልጣኞችን ከመሰረታዊ የግንኙነት ክህሎቶች እስከ የስልካቸውን ቅንብር መቀየር የሚደርሱ ውስብስብ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ የሚያስችል መንገድ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። ምንም እንኳን ይህ ማዕቀፍ የዚህን የስልጠና መርጃ ስብስብ አጠቃላይ ሂደት የሚመራ ቢሆንም፣ እያንዳንዱ የሥልጠና ክፍለ-ጊዜ ራሱን ችሎ እንዲቆም ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። ይህም አሰልጣኙ ትኩረት ለተደረገባቸው ሰልጣኞች ምን ተገቢ ሊሆን ይችላል የሚለዉን መሠረት በማድረግ የትኞቹን ክፍለ-ጊዜያት መጠቀም እንዳለበት እንዲመርጥ ያስችለዋል።

ሰዎችን ከተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብ ጋር ለማስተዋወቅ WhatsApp፣ YouTube፣ Google ፍለጋ፣ Wikipedia፣ Facebook፣ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ፣ Android፣ የተደራሽነት ባህሪያት እና TikTok እንጠቀማለን። እንዲሁም ስለ በይነመረብ፣ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ እና መስማት የተሳናቸው ወይም አይነ ስውራን እንዴት በይነመረብን መጠቀም እንደሚችሉ አጠቃላይ መግቢያ እናቀርባለን። እንዲሁም ስለ በይነመረብ መግቢያ አቅርበናል፣ ስለ ደህንነት እና ወጪ ሽፋን ሰጥተናል። ይህም በአብዛኛዎቹ ሀገሮች ውስጥ እነዚህ አገልግሎቶች አግባብነት እንዳላቸው በሚያሳዩ የሸማቾች ጥናቶቻችን ላይ የተመሠረተ ነው።

ይህንን የመሳሪያ ስብስብ በአገርዎ ውስጥ ለመጠቀም ከፈለጉ፣ ለታዳሚዎ ተገቢ በሆነው ነገር ላይ መሠረት በማድረግ እነዚህን አገልግሎቶች ማሻሻል ሊያስፈልግ ይችላል። ይህ አስፈላጊ ከሆነ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበው እንዴት እንደሚሰራ መመሪያ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

እንዲሁም ይህ እንዴት እንደሚሠራ መመሪያ በዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ውስጥ ከሚገኙ መረጃዎች እና ምክሮች በተጨማሪ በርካታ አጋዥ ምሳሌዎችን ያካትታል። ሁሉም የዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ተጠቃሚዎች የሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎቻቸውን ለማሟላት ከዚያ እንዴት እንደሚሠራ መመሪያ ጋር በጣም ተያያዥ የሆኑትን ክፍሎች እንዲገመግሙ እና እንዲጠቀሙ እናበረታታለን።

# በዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ውስጥ ምን ተካቷል?

## ስለ በይነመረብ መግቢያ

በርካታ ሰዎች ስለ ስልክ በይነመረብ ቢሰሙም እንኳን ምን እንደሆነ አያውቁም። ሰዎች ስለ በይነመረብ የሚያነሷቸውን በጣም የተለመዱ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያግዙ አንዳንድ ቀላል ማብራሪያዎችን አካተናል።

## WhatsApp

WhatsApp ታዋቂ፣ ዓለም አቀፋዊ መልዕክት መላላኪያ አገልግሎት ነው። ከአጭር የጽሁፍ መልዕክት ጋር ተመሳሳይነት አለው ማለት የመልዕክት መላላኪያ ተግባራቱ ሰዎች በተወሰነ ደረጃ የሚያውቁት ነገር ነው ማለት ነው። WhatsAppን እንደ መጀመሪያ ስልጠና መጠቀም አሰልጣኞች ሰዎች በሚያውቁት ነገር ላይ መሠረት አድርገው በበይነመረብ አማካኝነት የሚደረግ ግንኙነትን እና ለዚያም የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ጥቅሞች እንዲያስተዋውቁ ያደርጋል።

## YouTube

YouTube ሰልጣኞች ቀላል፣ ሳቢ እንዲሁም በአንጻራዊነት ቁጥጥር በሚደረግበት የመስመር ላይ ከባቢ የበይነመረብ ይዘትን እንዲያገኙ ያስችላል። አሰልጣኞች ሰዎች ለድምጽ-ምስል ይዘት በሚያሳዩት ጉጉት ላይ በመመስረት የተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን እንዲያስተዋውቁ ያደርጋል።

YouTube በግንኙነት ችግሮች ምክንያት በሁሉም አካባቢዎች ላይ ጥቅም ላይ ለማዋል ላይገኝ ይችላል። ይህ በሚሆን ጊዜ፣ የYouTube ሞጁሉን መዝለልን ወይም ለማስኬድ አነስተኛ የአየር ሰዓት የሚፈልግ ሌላ የድምጽ/ምስል መተግበሪያን (ለምሳሌ፣ እንደ Google ምስል ፍለጋ ያለ የምስል ፍለጋ መተግበሪያን) መጠቀምን እንመክራለን።

## Google ፍለጋ

Google ፍለጋ ሰዎች ለፍላጎታቸው አግባብነት ያለው ይዘት በበይነመረብ ላይ እንዲያገኙ ይፈቅዳል። ይህም ሰልጣኞች በበይነመረብ ላይ ለእነሱ የሚገኘው የመረጃ ስፋት እና ጥልቀት ላይ ተሞክሮ እንዲኖራቸው ያደርጋል። እንዲሁም የፍለጋ እና የአሰሳ ክህሎቶቻቸው ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ያስችላል። ተሳታፊዎቻቸውን በYouTube ሞጁል ላሳለፉ አሰልጣኞች፣ ይህ በYouTube የተሰጡ ክህሎቶች ላይ መሠረት እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣል።

## Wikipedia

Wikipedia ስለ ትምህርታዊ ጉዳዮች ገለልተኛ እና እውነተኛ መረጃን የሚያቀርብ ነፃ የበይነመረብ ማጣቀሻ (ወይም ኢንሳይክሎፔዲያ) ነው። ይህ ሞጁል ለሰልጣኞች አነስተኛ የስልክ አየር ሰዓት በሚጠቀም ድረ ገጽ ላይ ከበይነመረብ ላይ ሊገኝ የሚችልን ሰፊ መጠን ያለው መረጃ በምሳሌነት ያቀርባል። እንዲሁም በይነመረብ ላይ ያለ ይዘት አብዛኛውን ጊዜ በዓለም ዙሪያ ባሉ መደበኛ ሰዎች የተፈጠረ ነው የሚለውን ሃሳብ ያስተዋውቃቸዋል።

## Facebook

Facebook ሰዎች ከንግድ ዕውቂያዎች ጋር እንዲገናኙ፣ ዜናዎችን እንዲያገኙ፣ ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያስቀጥሉ ወይም ዝነኞችን እና የስፖርት ቡድኖችን እንዲከተሉ የሚያስችል ማህበራዊ አውታረ መረብ ነው። ይህ ሞጁል በማህበራዊ አውታረ መረብ ላይ የቀረቡ ሰፊ መጠን ያላቸውን አማራጮች ያሳያል እንዲሁም ስለ መለያ እና ይዘት ማጋራት ግንዛቤ ይሰጣል።

# በዚህ የስልጠና መርጃ ስብስብ ውስጥ ምን ተካቷል?

## Android

Android የሚሰራባቸው መሣሪያዎች በዓለም ዙሪያ ባሉ በርካታ ሰዎች በስፋት ጥቅም ላይ ይውላሉ። Android መሣሪያዎች ሰልጣኞች የተሟላ የበይነመረብ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ይህ ሞጁል በቀደሙት ሞጁሎች ላይ የተመሠረተ ነው፣ በAndroid መሣሪያዎች (ለምሳሌ፣ Google ረዳት) በኩል የሚገኙ በርካታ የላቁ የበይነመረብ አገልግሎቶችን ያቀርባል እንዲሁም ገንዘባቸውን መቆጠብ ወይም ደህንነታቸውን መጠበቅ የሚያስችሉ ቅንብሮችን ጨምሮ ሰልጣኞች መሣሪያዎቻቸው እንዴት ማቀናበር እንደሚችሉ (ለምሳሌ፣ የGoogle መለያ) ላይ የበለጠ ጥልቅ ግንዛቤ ይሰጣቸዋል።

## TikTok

TikTok በዓለም ዙሪያ ባሉ ወጣቶች ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ታዋቂነቱ እየጨመረ የመጣ ቪድዮ ማጋሪያ መተግበሪያ ነው። ይህ ሞጁል በTikTok እና በተመሳሳይ አገልግሎቶች ላይ የሚገኝ ሰፊ መጠን ያለው ይዘትን ለማሳየት እንዲያግዝ ከሌሎች ሞጁሎች (በተለይም ከYouTube) የተገኘውን ክህሎት መነሻ ያደረገ ነው። ሰልጣኞች ደህንነታቸው በተጠበቀ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ TikTokን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ግንዛቤ ይሰጣል። ለአንዳንድ ሰልጣኞች መተግበሪያውን ሲጠቀሙ የሚያዩትን ለምን እንደሚያዩ እንዲገነዘቡ ለማገዝ የስልተ ቀመር ጽንሰ-ሀሳብን ያስተዋውቃል።

## ተንቀሳቃሽ ገንዘብ

ተንቀሳቃሽ ስልክ ከፋይናንስ አካታችነት ቁልፍ መንገዶች አንዱ የሆነውን አንድ መንገድ ለተጠቃሚዎች ያቀርባል። ይህ ሞጁል ለሰልጣኞች የምዝገባ ሂደትን መረዳት፣ ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ አባል ገንዘብ መላክ፣ ክፍያ መክፈል እና መሠረታዊ የደህንነት አንድምታዎችን መረዳትን ጨምሮ ተንቀሳቃሽ ገንዘብን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ መሰረታዊ አጠቃላይ ዕይታን ያቀርባል። ይህ ሞጁል ብቻውን ወይም ከተቀረው MISTT ጋር መሰጠት ይችላል።

## ደህንነት እና ወጪ

ደኅንነትን መጠበቅ እና የተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብን የመጠቀም ወጪን መረዳት በእያንዳንዱ የWhatsApp፣ የYouTube Google፣ የWikipedia እና የFacebook ሞጁሎች ውስጥ ተካትቷል። ጥናታችን እንደሚያሳየው የተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብን ለሚጠቀሙ ሰዎች ደኅንነት እና ወጪዎች ዋነኛ ስጋት ናቸው፣ ስለዚህ እነዚህን በእያንዳንዱ ጥልቅ የሥልጠና ሞጁሎች ውስጥ እና በአጭር የሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎች ውስጥ በተናጠል ለማንሳት ወስነናል።

## የተደራሽነት ባህሪያት

ከዓለም ሕዝብ ውስጥ 15 በመቶ የሚሆኑት የተወሰነ ዓይነት የአካል ጉዳት ያለባቸው ናቸው። እንደ ትምህርት እና የጤና እንክብካቤ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ለማግኘት ተግዳሮቶች ሊያጋጥሟቸው ይችላል። ይሁን እንጂ ተንቀሳቃሽ ስልኮች ከእነዚህ ተግዳሮቶች የተወሰኑትን ለማስወገድ ያግዛሉ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ሊከብዷቸው የሚችሉ የዕለት ተዕለት ተግባሮችን እንዲያከናውኑ ያደርጋል። ይህ ሞጁል የማየት እና የመስማት እክል ያለባቸውን ሰዎች መርዳት ለሚፈልጉ አሰልጣኞች ምክር ይሰጣል።

ይህ ሥዕላዊ መግለጫ በሥልጠናው ውስጥ የተካተቱትን ቁልፍ አገልግሎቶች፣ ተግባራት እና ክህሎቶች ምስላዊ አጠቃላይ ዕይታ ያቀርባል።

# የተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብ

### WhatsApp
አንድ ለአንድ መልዕክቶችን መላክ እና መቀበል

ቡድኖችን መፍጠር እና መሳተፍ

### YouTube
ቪድዮዎችን መፈለግ

### Google
መረጃን መፈለግ እና ማሰስ

### Wikipedia
ነፃ መረጃን መፈለግ እና ማሰስ

### Facebook
ከጓደኞች እና ከቤተሰብ ጋር መገናኘት

### TikTok
ቪድዮዎችን መፈለግ

### Android
መረጃን መፈለግ እና ማሰስ

### ተንቀሳቃሽ ገንዘብ
የፋይናንስ አገልግሎቶችን በተንቀሳቃሽ ስልክ አማካኝነት

### ደህንነት
መስመር ላይ እንዴት ደህንነትዎ ተጠብቆ መቆየት እንደሚችል ማወቅ

### ተደራሽነት
የተደራሽነት ባህሪያትን በስልክዎ ላይ መጠቀምን ይማሩ

# ይህ የስልጠና መርጃ ስብስብ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል?

ከሰልጣኞችዎ ጋር ምን ያህል ጊዜ እንደሚኖርዎ የሚለያይ ሆኖ፣ ይህን ስልጠና መርጃ ስብስብ በተለያዩ መንገዶች መጠቀም ይችላሉ።

## 2-3 ደቂቃዎች

**ከሰልጣኞች ጋር በአንድ ጊዜ ከሁለት እስከ ሦስት ደቂቃዎች ብቻ ለሚኖራቸው አሰልጣኞች፣** ከሁለት እስከ ሦስት ደቂቃ የሚወስድ የሥልጠና ክፍለ-ጊዜ የያዘ አጭር ሥልጠና አለ። እያንዳንዱ ክፍል አንድን ርዕሰ-ጉዳይ ይሸፍናል። መምረጥ የሚቻልባቸው በርካታ ርዕሶች አሉ፦ ስለ በይነመረብ መግቢያ፣ WhatsApp፣ YouTube፣ Google፣ Wikipedia፣ Facebook፣ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ፣ Android፣ Ayoba፣ የተደራሽነት ባህሪያት፣ የመስመር ላይ ደህንነት እና TikTok።

**እንዲሁም አጭር ክፍለ-ጊዜያት ቀደም ሲል ሥልጠናውን ለጨረሱ ግን በተማሩት ላይ አጭር ማጠቃለያ ለሚፈልጉ ሰልጣኞች እንደ የማስታወስ ቆይታ ሊያገለግሉ ይችላሉ።**

## 45-60 ደቂቃዎች

**ከሰልጣኞቻቸው ጋር ከ45-60 ደቂቃዎች ለሚቆዩ እና ይበልጥ በተዋቀረ አውደ ጥናት ወይም የሥልጠና አካባቢ ውስጥ እያሳተፏቸው ላሉ አሰልጣኞች፣ ጥልቅ ሞጁሎቹ ለተመደቡበት የሰልጣኞች ቡድን የበለጠ ዝርዝር እና አጠቃላይ የሥልጠና ተሞክሮ ያቀርባሉ።**

እያንዳንዱ ጥልቅ ሞጁል ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን ይሸፍናል፦ ስለ በይነመረብ መግቢያ፣ WhatsApp፣ YouTube፣ Google፣ Wikipedia፣ Facebook፣ የመስመር ላይ ደህንነት፣ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ፣ KaiOS፣ Android፣ Ayoba፣ የተደራሽነት ባህሪያት እና TikTok። ደህንነት እና ወጪ በእያንዳንዱ የስልጠና ክፍለ-ጊዜ ውስጥ ተካትተዋል። እንደ የበይነመረብ መግቢያ ባሉ በጣም መሠረታዊ ሥልጠናዎች እንዲጀምሩ እና የሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎ የሚቆይበት ጊዜ በሚፈቅደው መሠረት የበለጠ ጥልቅ የሆኑ ሞጁሎችን እንዲቀጥሉ እንመክራለን።

# አጭር ሥልጠና

2-3 ደቂቃዎች

## አጭር ሥልጠናን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

**ይህ ክፍል ከሰልጣኞቻቸው ጋር ለመስራት ከሁለት እስከ ሦስት ደቂቃዎች ብቻ ላሏቸው አሰልጣኞች ነው።** እንዲሁም ቀደም ሲል ሥልጠናውን ለጨረሱ ግን በተማሩት ላይ አጭር ማጠቃለያ ለሚፈልጉ ሰልጣኞች እንደ ማደሻ ሆኖ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

እያንዳንዱ ክፍል አንድን ርዕሰ-ጉዳይ ይሸፍናል። መምረጥ የሚቻልባቸው በርካታ ርዕሶች አሉ፡- ስለ በይነመረብ መግቢያ፣ WhatsApp፣ YouTube፣ Google፣ Wikipedia፣ Facebook፣ ደህንነት፣ ወጪ፣ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ፣ Android፣ የተደራሽነት ባህሪያት እና TikTok። እያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ ስልኩ ላይ ያለ አገልግሎትን ማብራራት እና ልምምድ ማድረግ ላይ ትኩረት ያደርጋል።

## እያንዳንዱ አጭር ክፍለ-ጊዜ ተመሳሳይ መዋቅርን ይከተላል፡-

### ይህ ምንድን ነው?

ስለ አገልግሎቱ አጭር ማብራሪያ ይስጡ። **«ትምህርተ-ጥቅስ»** ምልክቶች አሰልጣኙ ሊናገሩ የሚችሉትን ይጠቁማሉ።

### ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

የአገልግሎቱን ጥቅሞች በአጭሩ ያብራሩ። **«ትምህርተ-ጥቅስ»** ምልክቶች አሰልጣኙ ሊናገሩ የሚችሉትን ይጠቁማሉ።

### እንዴት ነው የሚሰራው?

**በተግባር ያሳዩ!**

ሰልጣኞች በስልክ ላይ ያሉ አገልግሎቶችን እንዲጠቀሙ ለማገዝ «እንዴት መጠቀም እንደሚቻል» ፖስተሮችን ይጠቀሙ። ይህ እርስዎ የሚያቀርቡት ወይም የሰልጣኙ የራሳቸው ስልክ ሊሆን ይችላል።

### ልምምድ ያድርጉ!

ለሰልጣኞችዎ ተገቢ በሆኑ ምሳሌዎች **ልምምድ ያድርጉ**።

# ጥልቅ ሥልጠና

## ሥልጠናዎን እንዴት መንደፍ እንደሚችሉ

እነዚህ ጥልቅ ሥልጠናውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰጡ ምክሮች ናቸው።

### የነጠላ-ፆታ ክፍለ-ጊዜዎች

ወንዶችንና ሴቶችን በተለያዩ የሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎች ይከፋፍሏቸው። ይህ ለተግባራዊ ተሞክሮ እኩል ዕድልን እና የሥርዓተ-ፆታዊ ፍላጎቶች እና ስጋቶች ላይ በግልፅ ለመወያየት ቦታን ይሰጣል።

### የአነስተኛ ቡድን ልምምድ

ሰልጣኞችን ከስድስት የማይበልጡ ሰዎችን ወደሚይዙ አነስተኛ ቡድኖች ይከፋፍሉ። እያንዳንዱን ቡድን የሚደግፍ አንድ አሰልጣኝ ያቅርቡ። ይህ ሰልጣኞች የተግባር ልምድ እንዲቀስሙ ያስችላቸዋል እንዲሁም አቻ-ለአቻ ትምህርት እና ድጋፍ እንዲኖር ያደርጋል።

### የክህሎት ደረጃ ቡድኖች

ሰልጣኞችን ከሌሎች ተመሳሳይ የዕውቀት እና የልምድ ደረጃ ካላቸው ጋር ያጣምሩ። ሰልጣኞች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማቸው እና ፍላጎት እንዲያድርባቸው ቡድናቸው ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ጋር በተመሳሳይ የክህሎት ደረጃ ላይ መሆናቸው አስፈላጊ ነው። ሰልጣኞች በቡድኖቻቸው ውስጥ ካሉ ሌሎች ጋር ተመሳሳይ የክህሎት ደረጃ ላይ አለመሆናቸው ግልጽ ከሆነ ሥልጠናው ከተጀመረ በኋላ ሰልጣኞችን ወደተለያዩ ቡድኖች ለማዘዋወር አያመንቱ።

### የሚጋሩ መሣሪያዎች

ሰዎች የራሳቸው ስማርት ስልክ ከሌላቸው፣ የአየር ሰዓት ቀድሞውኑ የተጫነባቸውን የጀማሪ ደረጃ ዘመናዊ ስልኮችን ያቅርቡ። ስልኮቹ ተመሳሳይ መሆናቸውን (ለምሳሌ፣ ተመሳሳይ ስርዓተ ክወና እንዳላቸው) እና ተመሳሳይ ተግባራዊነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ይሞክሩ። ይህ በስልጠናው ውስጥ ሁሉም ሰው ወደ ተመሳሳይ እርምጃዎች ለማለፍ እና የግል የአየር ሰዓትን ስለመጠቀም እና የግል መረጃን ስለማጋራት የመሳሰሉ ስጋቶችን ለማሸነፍ ያስችላል። የሚቻል ከሆነ፣ በአንድ መሣሪያ ላይ ከሦስት ያልበለጡ ሰልጣኞች እንዲሆኑ እንመክራለን።

ጥልቅ ሥልጠና፡-

**መግቢያ**

# ለአሰልጣኞች ጠቃሚ ምክሮች

## ከመሠረታዊ ነገሮች ይጀምሩ

ምንም እንኳን ሰልጣኞቹ የተወሰኑ የበይነመረብ አገልግሎቶችን ቢያውቁም በዕውቀታቸው ላይ ክፍተት ይኖርባቸዋል።

## ቀላል ያድርጉት

አጭር እና ቴክኒካዊ ያልሆኑ ማብራሪያዎችን ይጠቀሙ።

## ጠቃሚ ያድርጉት

ሰልጣኞች ፍላጎት እንዳሳደሩ እንዲቆዩ የግል ፍላጎቶቻቸውን ይጠቀሙ።

## በተግባር ማዋልን ያበረታቱ

ሰልጣኞች በስልክ መለማመዳቸው ላይ ያተኩሩ።

## ሰልጣኞችን ያበረታቱ

ለሰልጣኞች በየጊዜው አዎንታዊ ማበረታቻዎችን ይስጧቸው። ለሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎ ተስማሚ ከሆነ፣ ለሰልጣኞች የምስክር ወረቀቶች ሊሰጣቸው ይችላሉ።

## ከሰልጣኞች ጋር መስተጋብር ይፍጠሩ

በሰልጣኞች እና በአሰልጣኞቻቸው መካከል የሁለትዮሽ መስተጋብርን ያበረታቱ።

# ጥልቅ ሥልጠናን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

**ይህ ከሰልጣኞቻቸው ጋር ከ45-60 ደቂቃዎች ለሚቆዩ አሰልጣኞች የሚሆን የጥልቅ ሥልጠና መመሪያ ነው።**

**45-60 ደቂቃዎች**

በመግቢያ ክፍለ-ጊዜ ጀምሮ አንድ ርዕስን የሚሸፍኑ የሥልጠና ክፍለ-ጊዜዎችን ያስከትላል፡- WhatsApp፣ YouTube፣ Google፣ Wikipedia፣ Facebook፣ የመስመር ላይ ደህንነት፣ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ፣ Android፣ የተደራሽነት ባህሪያት እና TikTok። ደህንነት እና ወጪ በእያንዳንዱ የስልጠና ክፍለ-ጊዜ ውስጥ ተካትተዋል።

ሥልጠናው የተዘጋጀው እያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ በቀደመው ላይ እንዲመሠረት ተደርጎ ቢሆንም እያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜም ራሱን ችሎ መሰጠት ይችላል። ይህም ለሰልጣኞችዎ ተገቢ የሚሆነውን መነሻ በማድረግ፣ መጠቀም የሚፈልጉትን የሥልጠና ክፍለ-ጊዜ መምረጥ ይችላሉ። በግንኙነት ችግር ምክንያት YouTubeን በአካባቢዎ መጠቀም የማይችሉ ከሆነ፣ ይህን ሞጁል መዝለል እና ሌላ ለማስኬድ አነስተኛ የአየር ሰዓት የሚጠቀም የድምፅ-ምስል አገልግሎትን መጠቀም ይችላሉ።

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱት የሰዎች ምስሎች እና ምሳሌዎች ከሕንድ በተለይም ከማሃራሽትራ ግዛት ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህን መመሪያ በሌሎች ቦታዎች ላይ ለመጠቀም ከፈለጉ፣ ለአካባቢዎ ተስማሚ የሆኑ የራስዎን ምሳሌዎች እና የሰዎች ምስሎችን እንዲያካትቱ እንመክራለን።

# የሥልጠና ክፍለ-ጊዜ የማረጋገጫ ዝርዝር

**ከእያንዳንዱ የሥልጠና ክፍለ-ጊዜ በፊት፣ ለመዘጋጀት ለራስዎ በቂ ጊዜ መስጠትዎን ያረጋግጡ። ተንቀሳቃሽ ስልኮቹን ለማቀናበር እንደሚያስፈልግዎ ከሚያስቡት በላይ በቂ ጊዜ መስጠትዎን ያረጋግጡ።**

- ለክፍለ-ጊዜዎ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በሙሉ እንዳሉዎት ያረጋግጡ (የእያንዳንዱ ሞጁል አጠቃላይ ዕይታ ገጽ ላይ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይመልከቱ)።
- ሁሉም ስልኮች ቻርጅ መደረጋቸውን ያረጋግጡ።
- በስልኮቹ ላይ ለመጠቀም የሚያቅዷቸውን ሁሉንም አገልግሎቶች ያውርዱ እና ያቀናብሩ።
- የሚጠቀሙባቸው ሁሉም የስልክ ቁጥሮች ሥልጠናው ላይ ጥቅም ላይ በሚውሉ ሁሉም ተንቀሳቃሽ ስልኮች ማስቀመጥዎን ያረጋግጡ።
- ለተሳታፊዎች ስልኩን ከመስጠትዎ በፊት ሁሉንም የግል የአየር ሰዓት ያጽዱ (ለምሳሌ ፎቶዎች፣ መልዕክቶች፣ ወዘተ)።
- የሥልጠና ይዘትዎን ይረዱ።
- የስልክ በይነመረብን በሁሉም ስልኮች የተንቀሳቃሽ ስልክ አውታረ መረብ አቅራቢ ጋር በመነጋገር እንዲሰሩ ያድርጉ (ይህ የተወሰኑ ቀናትን ሊወስድ እንደሚችል ያስታውሱ)።
- ለስልክዎችዎ ስም ይስጡ። በስልጠናው ወቅት ለይተው ማወቅ እንዲችሉ በእያንዳንዱ ስልክ ጀርባ ላይ ስሙን እና የስልክ ቁጥሩን የያዘ መረጃ ይለጠፉ።
- ግንኙነትዎን ይፈትሹ – MiFi/Wi-Fi እየተጠቀሙ ከሆነ እየሠሩ መሆናቸውን እና ሁሉም ስልኮች በመለያ መግባታቸውን ይፈትሹ።
- የተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብ የአየር ሰዓትን በሁሉም ስልኮች ላይ ይጫኑ።

## ጥልቅ ሥልጠና አራት ዋና ዋና የእንቅስቃሴ ዓይነቶችን ይይዛል፡-

**ማብራሪያ፡-**
የአገልግሎት ጥቅሞችን ለማስተዋወቅ ያለ አጭር ማብራሪያ

**ልምምድ፡-**
በስልኮች ላይ ተግባራዊ ልምምዶች

**ውይይት፡-**
ሰልጣኞች በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ እንዲያጤኑ ለማበረታታት

**ማጠቃለያ፡-**
የእያንዳንዱን ሞጁል ትምህርቶች ለማጠናከር